# ብሔራዊ የማዳበሪያ ፖሊሲ

ጥቅምት 1986 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ


| | |
|---|---|
| ክፍል አንድ፡ መግቢያ | 1 |
| ክፍል ሁለት፡ ዓላማዎች | 3 |
| ክፍል ሶስት፡ የገበሬዎች የማደበሪያ ፍላጐት እውነታ | 5 |
| ክፍል አራት፡ የማደበሪያ አቅርቦት | 7 |
| ክፍል አምስት፡ የማደበሪያ ስርጭትና ሽያጭ | 11 |
| ክፍል ስድስት፡ የማደበሪያ ዋጋ ትመናና ድጐማ | 13 |
| ክፍል ሰባት፡ የማደበሪያ ብድር | 14 |
| ክፍል ስምንት፡ የግብርና ምርምርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት | 15 |
| ክፍል ዘጠኝ፡ የማደበሪያ ጥራት ቁጥጥርና የአከባቢ ጥበቃ | 18 |
| ክፍል አስር፡ የብሔራዊ ማደበሪያ ኢንዱስትሪ አደረጃጀት | 20 |

# ብሔራዊ የማዳበሪያ ፖሊሲ

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. ግብርና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዋንኛ መሠረት ነው። ቅይጥ አስተራረስና (Mixed farming) በእንስሳት እርባታ ላይ ብቻ የተመሠረተ የማምረት ተግባር በኢትዮጵያ ደጋማና ቆላማ መሬቶች ላይ እንደቀደም ተከተላቸው የጐሉ ናቸው። የቅይጥ አስተራረስ ዘዴ ለዘመናት በመካሄድ ላይ ልምድ ነው። ለዚህም ምክንያቱ በእንስሳት እርባታና በአዝርዕት ልማት መካከል ባለው መደጋገፍ ሰቢያ አንዱ ለሌላው የሚሰጠው ድጋፍ ለጋራ ህልውናቸውመሠረታዊና ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ ነው። ቅይጥ እርሻዎች በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች የዕፅዋት ንጥረ ነገር ኡደት አሁንም ቢሆን የቅይጥ እርሻ ልማት ስርጭት የማይነጠል አካል ነው። ምንም እንኳን በቅይጥ እርሻ አከባቢዎች የተጨናነቀ የግብርና ልማት ልምድ ቢኖርም አሠራሩ አሁንም ምርታማነው። ስለሆነም ተስማሚና አደዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማስፋፋት ልምዱን መደገፍና ማጠናከር ያስፈልጋል።

2. በአሁኑ ጊዜ ያለው የእህል ምርት የሕዝቡን የምግብ ፍላጐት የሚያሟላ አልሆነም። ሂደቱም ቢሆን የሚያሰየው የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ እንደሚሄድ ነው። ስለሆነም ይህ ሁኔታ ለአስከፊ የምግብ እጥረት መከሰት አስተዋጽኦ ይኖረዋል። የምግብ እጥረት ችግሮችን ለመቀነስና በመጨረሻ ሙሉ ለሙሉ ለማስወገድ የግብርናን ምርታማነት በአጠቃላይና፣ በተወሰነ የመሬት ስፋት በጐሉ መልኩ ማሰደግ ይገባል። ከዚህ አንፃር፣ የማደበሪያዎች አጠቃቀምን ጨምሮ፣ አዲስና የተሻሻለ ቴክኖዋሎጂ ማሰራጨትና ተቀባይነት እንዲያገኙ ማድረጉ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በለፉት /20/ ሃያ አመታት የማደበሪያ ፍጆታ እያደረገ በመምጣቱ ምክንያት ለእህል ምርት ማደግ አስተዋጽኦ ያደረገ ሲሆን ከተሻሻለ ዘልማደዊ ዕውቀት ጋር የማደበሪያ አጠቃቀም ሲታከልበት፣ ማለት እስከሁን ማደበሪያ ከሚጠቀሙ አከባቢዎች ውጪ ስርጭቱን በስፋትና በተጠናከረ ሁኔታ ማካሄድ ለግብርና ምርት ማደግ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

3. የተዛቡ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች፣ ደካማ መሠረተ ልማት፣ የግብይት ስርዓት መዛጋትና ማዕከለዊ ቁጥጥር ያለበት የዋጋ ትመና የግብርና ምርትና ምርታማነትን፣ እንዲሁም የገበሬውን ማኅበረሰብ ገቢ ከገቱት ዋንኛ መሰናክሎች ጥቂቶቹ ናቸው። ይኼ ደግሞ በማደበሪያ አጠቃቀም ላይ አስከፊ ተጽዕኖ ያሰድራል። ምክንያቱም የማደበሪያ አቅርበት የተሟላ ቢሆንም እንኳን የገበሬው የመግዛት አቅሙ ስለሚደከም አጠቃቀሙንም ይ ጐዳል። ስለዚህ በገበያ አስተሰሰብ የታቀደ ፖሊሲዎቻችን ለሚያራምድ መንግስት፣ የተጠናከረ የኤክስቴንሽንና የብድር አገልግሎቶችን ማስፋፋቱ የገበሬውን ምርታማነት ለማሰደግ፣ እንደማነቃቂያ ይረዳል። በአንፃሩም፣ የአነስተኛ ባለሀብቶች የተደከመ የመግዛት አቅምም ያሰድጋል።

4. ማደበሪያን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣ በዋጋ ትመና፣ በስርጭትና ሽያጭ ረገድ የፖሊሲና መመሪያ አለመኖር፣ እንዲሁም የምርምር መረጃዎች ውስንነት፣ የጥሬ ሀብትና አገልግሎት አናሳነት፣ ደከማ መሠረተ ልማት፣ ለተፈጥሮ ሀብት ያለ የተዛባ አጠቃቀም፣ የቀድሞው ማዕከላዊ የዋጋ ፖሊሲ፣ የመረጃዎች ስርጭት አናሳነት፣ እንዲሁም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የአየር ሁኔታ መዛባት ለግብርናው ዘርፍ በተደከመ ሁኔታ መገኘት አስተዋጽኦ ያደረጉ ነጥቦች ናቸው።

5. የማደበሪያዎችን አትራፊነት ላቅ ማድረግ የሚቻለው፣ የተሻሻሉ ዘሮች፣ በቂ ውሃና የመሬት አያያዝ እንዲሁም ጉልህ ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴዎችን አጣምረን ስንጠቀም ነው። ስለሆነም የቴክኖሎጂ ፖኬጆች /በመከራተረጋግጠው የተቀመሩ እውቀቶች/ መዳረስ፣ የማደበሪያ አጠቃቀምንለማስፋፋት ይረዳል። ሆኖም የተሟላ የቴክኖሎጂ ፖኬጅ ዝግጅት በሌለበት ሁኔታም ቢሆን ባለው ተፈጥሮአዊ የለምነት ሁኔታ የአከበቢ ዝርያዎች አጠቃቀምን ማደፋፈርና ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ እድገት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ፣ በዘር ኢንዱስትሪ ፣ በግብርና ምርምር፣ በዕፅዋት ጄኔቲክ ሀብት፣ በደን፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በኬሚካል ኢንዱስትሪ እንዲሁም በማዕድንና ኢነርጂ በኩል ፖሊሲዎችና መመሪያዎች እየወጡና በመውጣትም ላይ ናቸው። በተጨማሪም በንግድ ንኡስ ዘርፍም መንግሥት የጅምለና የችርቻሮ ሽያጭ በግል እንዲካሄድም ዕድሉን ከፍቷል። እንዲህ ያሉ ወሳኔዎች ደግሞ በማደበሪያ አጠቃቀምና የመጠን ዕድገት ላይ በጐ ተጽእኖ ይኖራቸዋል። ስለሆነም የንዑስ ዘርፍን እድገትና ልማት ይበልጥ ለማቀላጠፍና የሚመረትበትን ሥርዓት ለማመቻቸት፣ ብሔራዊ የማደበሪያ ፖሊሲ ማውጣቱ የማይታለፍ ሆንዋል።

## ክፍል ሁለት

## ዓለማዎች

**ዋና ዋና ዓለማዎች ፤**

6. በተጠሰኑ የመሬትን መጠን ምርታማነትን በጉልህ ደረጃ ለማሳደግና ለማያቋርጥ የግብርና ስርዓት እድገት የማዳበሪያ ንዑስ-ዘርፍ ጠቀሜታ ብዙም አጠያያቂ አይደለም። በእርግጥ ይህ ደግሞ አርጋኒክና ኢንአርጋኒክ የሆኑ ማደበሪያዎችን በስፋትና አግበብ በለው ሁኔታ መጠቀምን በመጋበዝ፣ በተራው ጤናማ የሆነ የማዳበሪያ ንዑስ-ዘርፍን እድገት ይሻል። የማዳበሪያጡን ንዑስ-ዘርፍ ከሌሎች ምቹ ሁኔታዎች ጋር የማሳደጉ ጉዳይ፣ ብሔራዊ የምግብ ክምችት ግበችን ለማሟለት፣ ለኢንዱስትሪና ለውጪ ንግድ የሚሆኑ የእህል ምርቶችንም ለማሳደግ በመሰሪያነት ያገለግለል።

7. ብሔራዊ የምግብ ክምችትና በምግብ እራስን የመቻል ግበቹ ዕውን ሊሆኑ የሚችሉት ደግሞ በጥንቃቄ የታቀዱና የተቀየሱ የግብርና ልማት መርሐ-ግብሮችን ማራመድ ሲቻል ነው። ይህ ደግሞ በግልጽ የሰፈረ የማደበሪያ ፖሊሲና በሰፊው ገበሬ እውነተኛ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የማዳበሪያ አቅርቦት፣ ስርጭትና ግብይት፣ ዋጋና ድጎማ፣ ብድር፣ ምርምርና ኤክስቴንሽን፣ የጥራት ቁጥጥርና የአከበቢ ሁኔታ እንዲሁም ድርጅታዊ መዋቅርን ያከተተ ማስፈጸሚያ ፖሊሲ ያስፈልገዋል። ስለሆነም ይህን ግብ ለመጨበጥ ሲበል የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ያካተተ ብሔራዊ የማዳበሪያ ፖሊሲ ተቀርጿል።

**ዝርዝር ዓለማዎች**

ሀ. ለአነስተኛ ባለይዞታዎች በተፈለገው መጠን፣ ዓይነትና ጊዜ፣ እንዲሁም ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ የማደበሪያ አቅርበት መኖሩን ለማረጋገጥ፣

ለ. የገበሬጡን እጡነተኛ የማዳበሪያ ፍላጌት ለማሳደግ፣ በስነፍጥረትና ስነዕፅዋት ሀብታችን መስተጋብር በማደበሪያ አቅርበት ፤ በተስተካከለ ስርጭትና የግብይት ስርዓት፣ ተገቢ ማነቃቂያ ከመኖርና፣ የግብርና ምርትን ለማሰደግም የተሻሻለና የፈረቃ አስተራረስ ዘዴን አጠቃቀምን ማቀናጀቱም ለምግብ ክምችት፣ ለጥሬ ሀብት አቅርበትና ለውጭ ንግድ ሰብሎች በልተቋረጠ ሁኔታ የማሟለት ዓለማን ስለሚያግዝ፣

ሐ. ለብሔራዊ የምርምና የኤክስቴንሽን ሥርጭት፣ የቴክኖሎጂ ፓኬጆችን/ማለት የተሻሻሉ ዘሮች፣ መስኖ ልማት፣ የተቀናጀ የተባይ ቁጥጥር፣ የእርሻ መሣሪያዎች የተሻሻሉ የአስተራረስ ዘዴዎች ወዘተ/ በማመንጨትና በማስረጽ በኩል አስፈላጊውን እገዛ ለማድረግና በውጤቱም ፈጣን የሆነ የማደበሪያ አጠቃቀም እንዲሁም ያልተቋረጠ የግብርና ምርትና ምርታማነት እድገት፣ አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ፣

መ. በኢንኦርጋኒክና ኦርጋኒክ ማደበሪያዎች በኩል ሕጋዊና አግባብ ያለው አጠቃቀምን ለማበረታታት፣ በሀለዊውን የአፈር አጠቃቀም ልምድ በማሻሻል የግብርና ምርታማነትን ባልተቋረጠ ሁኔታ ለማሳደግ፣ የማደበሪያን ጥቅም የተረዱ ግን በማደበሪያ አቅርቦትና በፋይናንስ ምንጭ አለመሟላት ከመግዛት የታቀቡ አነስተኛ ባለይዞታዎችን ለማበረታታት፣ እንዲሁም እስከዛሬ የማደበሪያ ቴክኖሎጂ ለልደረሰባቸውና፣ ራቅ ባሉ አከባቢዎች የሚኖሩትን ተጠቃሚዎች ለማስተማር፣

ሠ. ተከታታይነት ያለው ውድድርና ብቃትን የተላበሰ ማደበሪያን ከውጪ የማስገባትና የሽያጭ ስርዓት በመፍጠር ያልተቋረጠ የማደበሪያ አቅርቦት መኖሩን ለማረጋገጥ፣

ረ. ለሀገር ውስጥና ለአካባቢው ፍጆታ የሚውሉ ማደበሪያዎችን /ኢንኦርጋኒክና ኦርጋኒክ/ በሀገር ውስጥ አምርቶ ለመጠቀም፣ የአፈሩን ይዘት ለማጐልበት፣ የአከባቢ ጥሬ ሀብቶችን በማልማት ረገድ ፍተሻና ግምገማ ለማነቃቃት፣

ሰ. የማደበሪያዎች /ኦርጋኒክና ኢንኦርጋኒክ/ እና የሌሎች የአፈር ይዘት ማሻሻያ ቁሶችን መፈብረኪያ ሆእርሻዎችን (Manufacturing Plants) ተቋሞች እንዲቋቋሞ ለማበረታታት፣

ሸ. ከአካባቢ ብክለ ነፃ የሆነና የጒላ የማደበሪያ አጠቃቀምን በመፍጠር፣ የተጠናከረ የጥራት ቁጥጥር አሰራር የሚኖርበትን ስርዓት ለመዘርጋት፣ እንዲሁም፣

ቀ. የማደበሪያውን ንዑስ-ዘርፍ ለማሳደግ የሚያስችል ተግባራዊና ብቃት ያለው ድርጅታዊ ማዋቅር በመፍጠር፣ ብሔራዊ የማደበሪያ ፖሊሲዎችን ተግባር ላይ ማዋል ይሆናል።

## ክፍል ሰስት

## የገበሬዎች የማደበሪያ ፍላጐት እውነታ

8. ምንም እንኳን የማዳበሪያ ፍጆታ በዓመት 12 በመቶ ቢያድግና፣ ወቅታዊና ለግለዊ ፍጆታዎችም የማይናቅ ቢሆንም /85 በመቶ በዋነኛው የምርት ወቅት /መኸር/ ከዚህ ውስጥ 80 በመቶው ደግሞ በሰስት ክፍሎች ጥቅም ላይ ይገኛል። በኢትዮጳያ ማደበሪያን መጠቀም የተጀመረው በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ሲሆን አሁንም ቢሆን በማንኛውም መለኪያ በጣም ዝቅተኛ ነው/ ያደገውመ አዝጋሚ በሆነ የጊዜ ሃደት ነው። ስለዚህ የገበሬውን እውነተኛ የማደበሪያ ፍላጐት ለማሰደግና ለማነቃቃት ልዩ ትኩረት የሚሹ በርካታ ጉደዩችም አለ። እነዚህ ተጠራራሽ የሆኑ ጉደዩች የማያከትቱት:-

ሀ. የተለያየ የተፈጥሮ ፀጋ /ለግብርና ምቹ የሆኑ የአየር ፀባይ ዞኖች/ እና የአፈሩ ስነ-ኬሚካለዊ ባህሪይ፣ የማደበሪያን አጠቃቀም ከማስፋፋት አንፃር፣

ለ. በአንድ በኩል በአስከሬ ሁኔታ የተጐዱ አፈሮች ለሚገኙባቸው ክልሎች ትክክለኛ የጥበቃ እርምጃዎች የመውሰድ አስፈላጊነት፣ በሌላ በኩል አፈሩ በመሟጠጥ ሂደት ውስጥ ባለባቸው ክልሎች የሚወሰድ የመከላከል እርምጃ፣ የማደበሪያ አጠቃቀምን ማስፋፋት ስለሚጋብዝ፣

ሐ. ክልሎች የመለያየታቸውን የሀል ካሁን ቀደም ማደበሪያዎች ተቀባይነት አግኝተው ለዓመታት ጥቅም ላይ በዋሉባቸውና በዚህም ሰቢያ ጥፋት በደረሰባቸው አካባቢዎች ያልተመዛዘነ አጠቃቀምን /ተጠስኖ የነበረ አጠቃቀምን ይጨምራል/ የማስተካከል አስፈላጊነት፣

መ. ከተሻሻሉ ዘሮች ዕጥረትና /95 በመቶ የሚሆኑ ገበሬዎች የራሳቸውን ዘሮች ነው የሚጠቀሙት/ ከሌሎች የቴክኖሎጂ ፓኬጆች አንፃር አነስተኛ በለይዘታዎች ማደበሪያን ቢጠቀሙ ይበልጥ ትርፋማ ስለማያደርጋቸው፣

ሠ. ለአዝርዕርት ምርት ጨሃ ዋንኛና ወሳኝ ጉዳይ እንደመሆኑ፣ አነስተኛና መከከለኛ ደረጃ ያላቸውን የመስኖ ግድቦችን ማስፋፋቱ፣ ማደበሪያ በመጠቀም ሊደርስ የሚችለውን ጉዳትና ጥርጣሬ ከመቀነሱ አንፃር፣

ረ. አዳዲስ የማዳበሪያ ተጠቃሚዎችን ቁጥር በአጠቃላይ ከማሳደግና፣ በተለይም ራቅ ያሉ የገጠር አካባቢዎችን ከማገዝ አንፃር፣ የኤክስቴንሽኑን ሥራ በልዩና በተጠናከረ መልክ ለማስፋፋት ቀደሚ የማስተማር ሂደትን በተለያዩ የማነቃቂያ ስልቶች መደገፍ ስለሚገበ፣

ሰ. በአቅርቦት በኩል ሙሉ በሙሉ ከውጭ በሚመጡ ማዳበሪያዎች ላይ ጥገኛ በመሆናቸው በውጪ ምንዛሪ እጥረት፣ በግዥ ስርዓት መጓተት፣ ወዘተ...አስከሬና ጸንተው የቆዩ ድክመቶቻችን በመሆናቸው፣

ሸ. ደኪማና ብቃት የሌለው የስርጭትና የግብይት ስርዓቶ በመኖሩ ሳቢያ ለገበሬዎች በተገቢው ሁኔታ ማደበሪያዎችን ለማቅረብና ለማከፋፈል በለመቻሉ፣

ቀ. የምርት ጨጤቶችንና የምርት ማሳደጊያዎችን ማዳበሪየን ጨምሮ አንጻራዊ ዋጋን የሚነኩ የዋጋ ፖሊሲዎች መኖራቸው በአጠቃለይ፣

በ. በግብርናዉ ዘርፍ የተጣሉ ግቦችን ለማሳካት የተነደፉ ብሔራዊ የግብርና ዓላማዎችና ስትራቴጂዎች ናቸው፣

9. በአጭርም ሆነ በረጅም ጊዜ እነዚህ ጉዳዬች የማዳበሪያ አጠቃቀምን የሚ ጎዱ ስለሆነ መንግሥት ተፃራሪ ሁኔታዎችን ለመቀነስ አግበብ ያለው እርምጃ እየወሰደ በ ጐ አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን ያበረታታል፣ ያግዛል፣

10. የፍላጐት ግምትና የሽያጭ ትንበያ፣ ሊቀርብ የሚገባጡን ትክክለኛ የማዳበሪያ አይነትና መጠን ለመወሰን ቁልፍ የሥራ አመራር ተግበሮች ናቸው። የፍላጐት ግምት ብዙ ጊዜ ትክክል ያልሆነ፣ በቢሮክራሲ ሰንሰለት የተተበተበ፣ ወቅታዊነቱንም ያልጠበቀና በውጤቱም የዋጋ ንረትና የእህል ምርት ቅነሰን የሚያስከትል ነው። ስለሆነም፣ በአስተማማኝ ሁኔታ ብሔራዊና ዓመታዊ፣ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የማደበሪያ ፍላጐትን ለማሟላት ተስማሚ የሆነ ተቋም ወይም ድርጅታዊ መዋቅር መዘርጋትን ይጠይቃል፣

## ክፍል አራት

## የማደበሪያ አቅርቦት
## ማደበሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገበት

11. ኢትዮጵያ ምንም እንኳን በበቂ መጠን ባይሆንም፣ ኢንኦርጋኒክ ማዳበሪያዎችን በሙሉ፣ ለውስጥ ፍጆታዋ ወደ ሃገር ውስጥ ታስገበለች። ስለሆነም ማደበሪያዎችን በበቂ መጠንና በወቅቱ ወደ ሃገር ውስጥ በማስገበቱ ረገድ ማነቆ ከሆኑት ምክንያቶች ዋንኞቹ (ሀ) የውጩ ምንዛሪ እጥረት፣ (ለ) ያልተሟላ የድርድር ሥርዓት /በከፊል የእርዳታ ሰጪዎችን አሠራር ይመለከታል/ የማዳበሪያ አቅርቦትን ማዘግየቱ፣ (ሐ) የወደብ መገልገያ ቁሳቁሶች እጥረት፣ በዚህም ሰቢያ በወደብ ውስጥ የመጫን፣ የማራገፍና የማንሰት አቅምን መቀነሱ፣ እንዲሁም (መ) ወደሃገር ውስጥ የሚገበው ማዳበሪያ በሙሉ በከረጢት ታሽጎ የሚቀርብ በመሆኑ የማደበሪያን ወጪ ከፍ ማድረጉ ናቸው። ስለዚህ እነዚህን ማነቆዎች በአግባቡ ለመውጣት መንግሥት የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስደል፣

ሀ. <u>የመዋዕለ ንዋይ ምደበ፣</u> መንግሥት እያደገ የመጣውን የሀገሪቱን የማዳበሪያ ፍላጐት ለማሟላትና በበቂና በለቂረጠ ሁኔታ መቅረቡን ለማረጋገጥ በቂ መዋዕለ ንዋይ ይመድበል። ይህ ማለት ደግሞ በፕሮግራም ለሚመራና ወቅቱን ጠብቆ ለሚደረግ የማደበሪያ ግብይት፣ መንግሥት በቂ የውጭ ምንዛሪ ይሰጣል። ከዚህም በለይ ለአጭርና መከከከለኛ ጊዜ የማደበሪያ አቅርበት፣ መንግሥት የገንዘብ ድጋፍ በወቅቱ እንዲገኝ ከለጋሾች /ብድርና፣ እርዳታ/ ጋር ድርድር ያደርጋል።

ለ. <u>የወደብ መገልገየ ቁሰቁሰችና አየያዝ፣</u> እነዚህን የመገልገያ ቁሳቁሶች የማሸሻሉና የማሰደጉ አስፈለጊነት፣ እያደገ ይመጣል ተብሎ ከሚገመተው የማደበሪያ መጠን አንፃር አንገብጋቢ ይሆናል። በቀጣዩቹ ዓመታት ይበልጥ አስቸጋሪ እንደሚሆንም ይጠበቃል። ስለሆነም መንግሥት ከሚመለከታቸው መንግሥታት ጋር የተለያዩ ድርድሮችን በማድረግ ለወደበች አቅምና መገልገያ ቁሳቁሶች መሟለትና መሸሻል ጥረት ያደርጋል፣

ሐ. <u>ማደበሪየን በብትን ጭነት መልክ ማስገበት፣</u> ባለፈውም ሆነ በአሁኑ ጊዜ ማደበሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት በከረጢት ታሽገው ሲሆን፣ በብትን-ጭነት መልክ የማስገባት ጉዳይ የሚያስገኘው ጥቅም የተረሳ ጉዳይ ነው። በብትን መልክ በብዛት የማስገባቱ ጠቀሜታ (i) ከአቅራቢ አገሮች ከፍተኛ የጉልበት ዋጋ ጥያቄ አንፃር፣ በከረጢት አሽጎ ለመጫን የሚወጣውዐ ወጪ በማስቀረቱ (ii) በባህር ላይ የጭነት መጫናነቅ መጠንን በመቀነሱ (iii) ራቅ ካሉ ሥፍራዎች ለማራገፍ ሲባል ለአጡራጆና ጫኞች የሚጠጣውን ከፍተኛ ወጪ በማስወገዱ (iv) ጊዜና ገንዘብን የሚቆጥብ፣ በጣም ፈጣን የሆነ የማራገፍ ስርዓትን ከመፍጠሩ እና (v) ማደበሪያን በማሸግ በኩል በየአካባቢው የሥራ ዕድል ለመክፈትና በሀገር ውስጥ የሚሰሩ ከረጢቶችንም ጥቅም ለይ ለማዋል በማስቻሉ ነው፣

12. በብትን-ጭነት መልክ የማስገባቱን ጠቀሜታ ለማስፋፋት፣ መንግሥት የታሸጉ ማዳበሪያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባቱን ሁኔታ በተቻለ ፍጥነት በማስቀረት አስመጪዎች ማዳበሪያን በብትን-ጭነት መልኩ እንዲያስገቡ ያደፋፍራል። ለዚህም ሲባል በመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅዶች ውስጥ በማራገፊያ ወደቦች አካባቢ የብትን-ጭነት ማዳበሪያዎችን ማስተናገድ የሚያስችሉ የመገልገያ ቁሳቁሶችን መጠንና ዓይነት ያሰድጋል። በተመሳሳይ ጊዜም ወደ ብትን-ጭነት አቅርቦት ለመሸጋገር እንዲቻል ጊዜያዊ ዝግጅት በማድረግ፣ ማዳበሪያን ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገቡ /ግምማአክና የግል/ በወደብ አካባቢ በከረጢት የማሸጉን ሥራ እንዲያከሂዱ ያበረታታል።

13. <u>ከውጭ በማስገበቱ ረገድ የኢኮኖሚ ድግፍ፣</u> በመንግሥት በኩል እየተወሰደ ያለውን አጠቃለይ የኢኮኖሚ ተሃድሰ፣ እንዲሁም አዲሱን የማደበሪያ ሽያጭ እስትራቴጂ በመከተል በውድድሩ ውስጥ የግል አስመጪዎች በወቅቱና በሚፈልገው መጠን የማስገበታቸው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ፣ እንደሀ ተቃሎ የሚታይ ስለልሆነ መንግሥት ይህን ዓይነቱን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። በኢንቨስትመንት፣ በመጋዘን አገልግሎት እና የብትን-ጭነት ማካሄጃ ቁሳቁሶች መሟሳታቸው ያረጋግጣል፣ ያበረታታል፣

14. <u>ማዳበሪያን ከውጭ የማስገባት ደረጃወች፣</u> ባለፈውም ሆነ በአሁኑ ወቅት ማደበሪያን ከውጭ የማስገበቱ ደረጃ በልዩ ሁኔታ ስለሆነ ዋናዎቹ የሽያጭና የማንሳት ጊዜያት ተቀናጅተው በቆጠራ ምክንያት የሚከሰቱ ወጪዎች ሊቀነሱ ይገባል። ስለሆነም መንግሥት የማደበሪያ ፍላጐት በማይኖርበት ወቅት አስመጪዎች በከፍተኛ መጠን ማደበሪየን ወደ ሃገር ውስጥ ለማስገበት የሚችሉበትን መርሃ ግብር እንዲነደፉ ያበረታታል፣

15. <u>ማደበሪየን በሀገር ውስጥ ማምረት፣</u> በሀገር ውስጥ ማዳበሪያን የማምረት እንቅስቃሴ ባለመኖሩ፣ ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ኢንኦርጋኒክ የሆነ የማደበሪያ ፍላጐትዋን የምታሟላው ከውጪ በማስገባት ነው። ስለዚህ ደረጃ በደረጃ ኦርጋኒክና ኢንኦርጋኒክ የሆኑ ማደበሪያዎች በሀገር ውስጥ የማምረት ችሎታ መኖሩን ማረጋገጥና ማበረታታት የመንግሥት ግዴታ ነው። ለዚህም መነሻው፣

ሀ. በመካከለኛና ረጅም ጊዜ በሰፋትና በፈጣን ሁኔታ እያደገ ይመጣል ተብሎ የሚገመተው አስተማማኝ የማደበሪያ ገበያ ሁኔታ፣

ለ. በተለያዩ ጥናቶችም እንደተረጋገጠው በሀገር ውስጥ የጥሬ-ሃብት ክምችት መኖር፣ እና

ሐ. የሀገር ውስጥና የውጭ ካፒታልን ለኢንቨስትመንቱ ለማሳለፍ ያለውን ችሎታ ከማጤን ሲሆን፣ መንግሥትም እያደገ የሚመጣውን የሀገሪቱን የማደበሪያ ፍላጐት ደረጃ በደረጃ በሀገር ውስጥ ምርት የመተከቱን አስፈለጊነት ስለሚያምንበትም ጭምር ነው፣

<u>የጥሬ ሀብት ክምችት፣</u> በአስተማማኝ ሁኔታ ማደበሪያን በሀገር ውስጥ ለማምረት ዋስትናው አስተማማኝ ጥሬ ሃብት በሀገር ውስጥ መኖሩ ነው። ሀገሪቱ ደግሞ የተለያዩ የማዕድናንና የሃይል ጥሬ-ሀብቶች እንዲሁም ተስማሚ አየርና ገጸ-ምድር ያላት ነች። በቂ የኃይል ሀብት ከመኖሩም በተጨማሪ ለልዩ ልዩ የማደበሪያ ምርት አይነቶች የሚያገለግሉ መጠነ ሰፊ የሆኑ የጥሬ ሀብት ክምችቶችና ሌሎች ለግብርና ሥራ ተስማሚ የሆኑ ማዕድናትም ይገኛሉ። ከዚህም በላይ የማይናቅ የጨው-ኃይል፣ የተፈጥሮ ጋዝ፣ ጂኦተርማል እና በተወሰነ መጠንም የከሰልና የነዳጅ ሃብቶችም አሏት፣

አነስተኛ ዋጋ ያላቸውንና አርጋኒክ የሆኑ የማደበሪያ ምርቶችን ለማልማት ያለው ክምችቶ፣ ከፍተኛ ቁጥር ካለው የእንስሳት ሀብታችንና ከቅይጥ የግብርና ምርት አስተራረስ ስርዓት አንፃር ሲታይ በጣም ከፍተኛ ነው። የግብርናና የኢንዱስትሪ ቅሪቶች፣ የቁራ ትርፍራፊዎችና የከተማ ቁሸሸች ሁሉ አስፈላጊ ጥሬ ሃብቶች ናቸው። ስለሆነም መንግሥት ጠለቅ ያለ የሀብት ግምገማ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ስለሚያምን በዚህም ረገድ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣

<u>ኬሚከለዊ ማደበሪየዎች፣</u> ከላይ እንደተገለጸው ሀገሪቱ ሙሉ በሙሉ ከውጭ በሚገቡ ኬሚከለዊ ማደበሪያዎች ላይ ጥገኛ ነች። ወደ ሃገር ውስጥ ለሚገቡ ማደበሪያዎች ግዥና የማጓጓዣ ተግበር የሚያስፈልገው የውጭ ምንዛሪ በጣም ከፍተኛ ሲሆን ወደፊትም ቢሆን የሚያድግ ነው። ያልተቋረጠ አቅርበት ደግሞ ከውጩ በማስገበት ብቻ የሚዘልቅ አይደለም። ስለዚህ ደረጃ በደረጃ ከውጭ የማስገበቱን እነቅስቃሴ ለመቀነስ በሀገር ውስጥ የማደበሪያ ማምረቻው እርሻዎችን ማቋቋሙ፣ ብሔራዊ ጥቅምና ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገበ ተግበር።

የናይትሮጅንና ፎስፈረስ ማደበሪያዎችን ለማምረት በሚደረገው እንቅስቃሴ ሊገኙ በሚችሉና ሀገረኛ ለሆኑ ጥሬ ሀብቶች ትኩረት ይሰጣል። መንግሥትም ቢሆን በሀገር ውስጥ የማደበሪያ ማምረቻ ሆርሽዎች እንዲቋቋሙ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት አስፈላጊና ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣

16. <u>በዮ ማደበሪየወች፣</u> ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸው አርጋኒክ ማደበሪያዎች፣ ከፍተኛ ዋጋ ካላቸው ኢንአርጋኒክ ማደበሪያዎች ጋር በተጨማሪነት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። የበዮጋዝን ዝቃጭና ሌሎች የግብርናና፣ አግሮ ኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶችን እንደ ማደበሪያ መጠቀሙም በጣም ርካሽና እጅግ ጠቃሚ ባዬ-ማደበሪያዎች በመሆናቸው ወደፊት በሰፊው ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል። ስለሆነም የአርጋኒክና በዩ ማደበሪያ ማምረቻ ተቋም፣ በግብርናና አግሮ ኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶች፣ በቁራ ትርፍራፊዎች እንደሁም በከተማ ቆሻሸች ላይ ተመስርተው እንዲቋቋሙ ግለዊና ሕዝበዊ ዘርፎች ኢንቨስት እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።

17. <u>የአፈር ይዘት ማሻሻያ ምርት፡</u> እጅግ ብዙና በሰፊው ተሠራጭተው የሚገኙ የአፈር ይዘት ማሻሻያ ጥሬ ሀብቶችን ለምሳሌ ኖራ /በሃ ድንጋይ/፣ ደሎማይት፣ ጂፕሰም ወዘተ...በሀገሪቱ ይገኛሉ። ስለሆነም በሕዝባዊና ግላዊ ዘርፎች ተሳትፎ የማምረቻ ተቋሞች እንዲቋቋሙ ይበረታታሉ። መንግሥትም የአፈር ይዘት ማሻሻያ ጥሬ ሃብቶችን ለሚያመርቱ የሀገር ውስጥ ማምረቻ ተቋሞች ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ የመሰረተ ልማት ግልጋሎቶችን ለማጠናከር ተገቢ እርምጃ ይወስዳል።

18. <u>የኢንቨስትመንት ሀብቶችን ማንቀሳቀስ፡</u> በማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት የተረጋገጠና ወሳኙ ነጥብ፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ካፒታልን እንዲሁም ሙያን ለዚሁ ሥራ ማሰለፍ ነው። መንግሥት በሚያራምደው የማክሮ-ኢኮኖሚ የለውጥ መንፈስና በሌሎች የውጥረት ማርገቢያ ፖሊሲዎች አማካኝነት፣ የውጭና የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ሙሉ በሙሉ የሀገር ውስጥ ማዳበሪያን በማምረቱ ሥራ እንዲ ሰተፉ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥራሉ።

## ክፍል አምስት
## የማደበሪያ ሥርጭትና ሽያጭ

19. የማዳበሪያዎች አቅርቦት/ከውጭ የገባም ሆነ በሀገር ውስጥ የተመረተውን/ እና ማደበሪያንና ሌሎች የምርት ማሳደጊያዎችን ለማስተዋወቅ የሚደረግ የተጠናከረ የምርምርና የኤክስቴንሽን አገልግሎት በተቀላጠፈ የስርጭትና ሽያጭ ሥርዓት እስከልተዘረጋ ድረስ ከንቱ መባዝን ይሆናል። ስለሆነም የስርጭቱ ስርዓት ሊያረጋግጥ የሚገባው:-

   ሀ. በንግድ ላይ የተመሠረተና የተደራጀ የማዳበሪያ ስርጭት መኖሩን ማረጋገጥ፣ ምክንያቱም ተጠቃሚዎቹ የማዳበሪያ አጠቃቀምን በደንብ ተገንዝበው በጡጡቱም ከፍተኛውን የኢኮኖሚ ጥቅም/ ማለት ምርትን ማሳደግ፣በተወሰኑ የመሬት መጠን ከፍተኛ ምርት የማግኘት ጥቅምን/ሊያገኙና የኑሮ ደረጃቸውንም ሊያሻሽሉ ይገባል፣

   ለ. ለአነስተኛ ባለ ይዞታዎች ማዳበሪያ በተፈለገው መጠን፣ ዓይነት፣ ጊዜና ተመጣጣኝ ዋጋ መቅረቡን ማረጋገጥ ይገባል። በአንጻሩም እ.ኤ.አ. ከ1992 ጀምሮ በማዳበሪያው ስርጭትና ሽያጭ ስርዓት ውስጥ ሰስት ዓይነት ተሰታፊዎች ይኖራሉ።

<u>ተሰታፊዎች</u>

   ሀ. <u>የግሉ ዘርፍ፣</u> እያደገ ከመጣው የማዳበሪያ ፍላጐትና ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ ሊሰራጭ ከሚታሰበው መጠን አንጻር፣ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ፣ በተለይ ለአነስተኛ በለይዞታዎች በወቅቱ ማቅረብና ዋጋውንም የመቀነሱ ነገር ወሳኝ ጉዳይ ነው። ስለሆነም መንግሥት የግሉ ዘርፍ ማደበሪያን ከውጭ በማስመጣቱ፣ በማሰራጨቱና በጅምለና በችርቻሮ ንግድ ውስጥም ሙሉ በሙሉ እንዲሰተፉ ያበረታታል።

   ለ. <u>የአገልግሎ ኅብረት ሥራ ማኅበራት፣</u> የገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለአባሎቻቸው የተሻለ አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት እንደለባቸው የታወቀ ጉዳይ ነው። ስለሆነም የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት በማዳበሪያ ንዑስ ዘርፍም እንዲሳተፉና ትክክለኛውን ማዳበሪያ በወቅቱና በተመጣጣኝ ዋጋ ከሌሎች መንግሥታዊና የግል ንግድ ተቋሞች ጋር በመወዳደር ለአባሎች እንዲያቀርቡ፣ ሊጠናከርና ሊበረታቱ ይገባል።

   ሐ. <u>የመንግሥት ሚናና ተሳትፎ፣</u> ቀደም ብሎ ማዳበሪያን ከውጭ የማስገባት፣ የማሰራጨትና የመሸጥ ተግባር በግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ኮርፖሬሽን በሞኖፖል ተይዞ ሲካሄድ ቆይቷል። ከመንግሥት የኢኮኖሚ ተሃድሶና የውጥረት ማርገብ ፖሊሲ /አዲሱን የማዳበሪያ የሽያጭ ስትራቴጂ ይመለከታል/ አንፃር የግምማአከን መዋቅር በማሻሻል በነጻው ገበያ ውስጥ ከግሉ ዘርፍና ከማኅበራት ጋር በውድድር መንፈስ እንዲሠራ ይስተካከለል። ድርጅቱ እራሱን ችሎ እንዲንቀሳቀስ ለዳይሬክተሮች በርድ ተጠሪ ይሆናል፣ ለዚህም አስፈላጊ የሆኑ ሀጐች ይታወጁለታል።

20. <u>የትራንስፖርትና የማከማቻ አገልግሎቶች፣</u> በሀገሪቱ የትንስፖርትና የማከማቻ አገልግሎቶች፣ ማደበሪያን በማሰራጨትና በመሸጥ ረገድ ዋንኛ ማነቆዎች ሆነው ቆይተዋል። ማደበሪያ ከወደብ ወደ ሀገር ውስጥ የሚጓጓዘው በየብስ በመሆኑ፣

ሀ. ማዳበሪያዎችን ከመርከብ ላይ በተመጣጣኝ ሁኔታ በመረከቡ ረገድ የጭነት መኪናዎች ችግር እጅግ አስከፊ ሆኖ ቆይቷል።

ለ. በወደቦችና በመሐል ሀገር የመጋዘን አገልግሎት እጥረት በመኖሩ፣ ማደበሪያን አላአስፈላጊ ለሆነ ብክነትና ዝርፊያ ደር ጌታል። በተጨማሪም፣

ሐ. የተበላሹ መጋቢና ዋና መንገዶች ባለመኖራቸው ሳቢያ ማዳበሪያን ለማዕከላዊ የሽያጭ ጣቢያዎች በወቅቱ ለማድረስም እንቅፋት ሆነዋል። ስለሆነም እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ፣ መንግሥት ፊዚካል መሰረተ-ልማቶችንና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማሻሻልና ለማስፋፋት ኢንቨስት ያደርጋል፣ የግሉ ዘርፍም በኢንቨስትመንቱ እንዲሰተፍ ያበረታታል፣ ይደግፋል።

21. <u>የማዳበሪያ መጠባበቂያ ክምችት፣</u> የመገናኛ አጨታሮች በደንብ ባልዳበሩበት፣ የማዳበሪያ አጠቃቀም ሙሉ በሙሉ የውጭ ጥገኛ በሆነበት፣ የማዳበሪያ አጠቃቀቀም እየደገ በለበትና የማዳበሪያ አቅርበትና ስርጭትም በዓለም የማዳበሪያ ፍሊጌት/ አቅርቦት ሁኔታ በሚወሰንበት፣ በተጨማሪም ዓለም አቀፍ ዋጋውም ተለዋዋጭ በሆነበት ሁኔታ፣ ወዘተ፣ ያለጥርጥር መጠነኛ የማዳበሪያ መጠባበቂያ ክምችት በመጋዘን ሊኖር ይገባል። ስለሆነም፣ መንግሥት በሀገሪቱ ስትራቴጂያዊ አከባቢዎች መጠነኛ የማዳበሪያ መጠባበቂያ ክምችት እንዲኖር እርምጃ ይወስዳል። ለዚህም የመጠባበቂያ ክምችት አጠቃቀም እንዲረደ፣ በዋጋና በአስተደደር ረገድ የአጠቃቀምና የአያያዝ መመሪያ ያወጣል።

## ክፍል ስድስት

## የማዳበሪያዎች ዋጋ ተመንና ድጎማ

22. የማዳበሪያ ዋጋ ትመና፡ የማዳበሪያ ዋጋ ትመና ዋንኛ ዓላማ፡ የተሟላ የማዳበሪያ አጠቃቀምና ለአራሹ ማኅበረሰብም የተረጋጋ የዋጋ ተመን እንዲኖር ለማድረግ ነው። ባለፈው ጊዜ የማዳበሪያም ሆነ የእህል ዋጋ /በቋሚነት የሚወሰን የእህል ዋጋና የኮታ ስርዓት ነበር/ በመንግሥት ይወሰን ስለነበረ፤ የእርሻ አምራቾች እንዳይነቃቁ አድርጓቸዋል። መንግሥት እንዲህ ያለው የዋጋ ትመና ስርዓት የማዳበሪያን ግብይት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የማይናጋ ከመሆኑም በላይ በማዳበሪያ፤ ንዑስ-ዘርፍ ነጻ የውድድር አሠራሩንም የማያስተጓጉል እንዲሆን ያጠናል። በመካሄድ ላይ ያለው የማክሮ ኢኮኖሚ ተሐድሶ /በተለይም የውጭ ምንዛሪ ማስተካከያ/ ከውጭ የሚመጣ ማዳበሪያዎችን ዋጋ በተከታታይ መንከቱ ስለማይቀር፣ መንግሥት ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ማዳበሪያዎች ላይ የሚፈጠረውን ለውጥ፤ማለት የማዳበሪያ ፍጆታ እድገትን፤ የግብርና ውጤቶችንና የማዳበሪያን አንፃራዊ የዋጋ ተመን፤ እንዲሁም ከክልል-ክልል የሚፈጠረውን የዋጋ አጠጣጥ ሥርዓት ይከታተላል፤ ይገመግማልም።

23. የማዳበሪያ ዋጋ ድጎማ፡ እስከዛሬ ቀጥተኛ የሆነ ድጎማ አይታወቅም። ምክንያቱም የግብርና ውጤቶችም ሆኑ የማዳበሪያ ዋጋ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ነበሩ። የሆነ ሆኖ መንግሥት በኢኮኖሚ ተሐድሶውና በገበያ ጥጥረት ማርገብ ፖሊሲው አማካኝነት ማዕከላዊ የዋጋ ትመና አሠራርን በገበያ ኃይል በሚገዛ የዋጋ አሠራር ስለለወጠው፤ በግብርና ምርት አምራቾችና፤ በግብርና ምርት ማሰደጊያ አቅራቢዎች መካከል የውድድር መንፈስን ይፈጥራል ተብሎ ይገመታል። ይሁን እንጂ ለአጭርና መካከለኛ ጊዜ የማዳበሪያ ድጎማ የግድ የሚሆኑባቸው ምክንያቶችም አሉ። ለእንደዚህ ያለው ድጎማ ምክንያቶች፤

ሀ. ወደፊትም ቢሆን ሊደረግ የሚታሰበው የውጭ ምንዛሪ ማስተካከያ ለውጭ፤ የሀገር ውስጥ የማዳበሪያ ዋጋን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያንር ስለሚታመንና ይሄም ከአነስተኛ ባለይዞታዎች አቅም በላይ ሊሆን ስለሚችል፤

ለ. ብሔራዊ የማዳበሪያ ዋጋ ተለዋዋጭ ስለሆነና ሊጨምርም ስለሚችል፤ የሀገር ውስጥ የማዳበሪያ ዋጋን ማረጋጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ሐ. በኢትዮጵያ የማዳበሪያ ፍጆታ እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑና ፍጆታውን መሰደጉም እጅግ አስፈላጊ ስለሆነና፤ ይልቁንም፤ በመጀመሪያዎቹ የማለማመጃ ወቅቶች፤ ገበሬዎችም ለከፍተኛ አደጋ ሊጋለጡ ስለሚችሉ እና

መ. በአንዳንድ ሁኔታዎችም የአጭር ጊዜ የዋጋ ግሽበትን ለማስተካከልም ጥቅም ላይ ሊውል ስለሚችል ነው። ስለሆነም እንግዲህ፤ የድጎማን ጥያቄ በአጭር፤ መካከለኛና ረጅም ጊዜ ውስጥ፤ ማዳበሪያ በልተቋረጠ ሁኔታ ለግብርና ምርታማነትና የአነስተኛ ባለይዞታዎችን ኢኮኖሚያዊ ተጨባጭ ሁኔታ ከማገዙ አንፃር ተዛምዶ ሊታይ ይገባል።

24. በድኅማ ረገድ ሊሆን የሚችለው የመንግሥት አቀራረብ፣

ሀ. የዋጋ ድኅማ ፖሊሲውን በጥብቅ የመቆጣጠርና የመከታተሉ አስፈላጊነት የሚመነጨው በግብርና ልማት ስትራቴጂያዊ ዓላማ መሰረት ያለቋረጠ የአዝርዕት ምርት ዕድገት ለማስገኘት፣ የምግብ ክምችት ለመፍጠር፣ የኢንዱስትሪ ጥሬ ሀብትና የኤክስፖርት ምርቶችንም ለማስገኘት፣ ሲሆን

ለ. ባለው ሁኔታ ውስጥም ድኅማን የማስቀረት ፕሮግራምም አጥኝም የማከሄድንም ይጨምራል።

<u>ክፍል ሰበት</u>

<u>የማደበሪያ ብድር</u>

25. የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም፣ ፈጣን የሆኑ የማደበሪያ አስመጪዎች፣ አሰራጮችና የጅምላና ችርቻሮ ሽጮች ተሰትፎን ይጠይቃል። መንግሥትም ቢሆን እነዚህን ክፍሎች አቅማቸውን ለማሰደግ እንዲችሉ በባንክ ተቋሞች የብድር ፖሊሲና የአሰራር መመሪያዎች እንዲታገዙ ያበረታታል።

26. ለአነስተኛ ባለይዞታዎች በቂ የብድር አገልግሎት መኖሩን ማረጋገጥ፣ ገንዘቡም የሚቀርብበትንና የሚመለስበትን የአሰራር ስልት መቀየሱ አስፈላጊ ጉደይ ነጡ። ሆኖም ለዚህ ሰስት ማነቆዎች /ችግሮች/ እንዳሉ ይታጠቃል። እነሱም

ሀ. በተለይ ለአነስተኛ ባለይዞታዎች በተለየ ሁኔታ የሚያገለግሉ የፋይናንስ ተቋሞች፣ አለመኖር

ለ. ለገበሬዎች የተሰጡ የማደበሪያ ብድሮችን ተቆጣጥሮ ማስመለስ የሚችል ብቃትና ችሎታ ያለው የገጠር ተቋም አለመኖር፣

ሐ. በገበሬጡ ስነ-ልቡናዊ አመለካከት በብድር የተሰጠ የመንግሥት ገንዘብ እርዳታ ነው ስለሚባል ስለመመለሱም አያስቡም ።

ስለዚህ እነዚህን ችግሮች ለመቀነስና አነስተኛ ባለይዞታዎችን ለመርደት ሲባል የሚቀየሰው የብድር ፕሮግራም

ሀ. ለአነስተኛ ባለይዞታዎች የማደበሪያ ብድርን የሚያስፋፉ የፋይናንስ ተቋሞች በገጠር መቋቋማቸውን፣

ለ. የኅብረት ሥራ ማኅበራትን፣ ሌሎች ማኅበራትና ቡድኖችን በማስፋፋትና በማደራጀት ማናቸዋንም ድጋፍ መስጠትና በማንኛጡም ደረጃ በማደበሪያ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሰተፉ ማበረታታትን።

ሐ. የሚፈለገውን የብድር መጠን በመገምገምና በወቅቱ ተመላሽ መሆኑንም በማረጋገጥ ረገድ ትክክለኛ አስተዳደርና ዲስፒሊን መኖሩን የሚያረጋግጥ ሊሆን ይገባል።

## ክፍል ስምንት

## የግብርና ምርምርና የኤክስቴሽን አገልግሎት
## የአፈር ለምነት ምርምር /ጥናት/

27. በአየሩ ሁኔታ፣ በጂኦሎጂና ተፈጥሮአዊ ገጽታ በሚታየው ሰፊ ልዩነት ሳቢያ ለተለያዩ የአፈር ዓይነቶች፣ በተለያዩ ባህሪ መፈጠር አስተዋጽኦ አድርጓል። በኢትዮጵያ ለእርሻ ተስማሚ ከሆኑት የአፈር ዓይነቶች ዋነኛው፣ ኒቶሰል (Nitosols) ሲሆን ከፍተኛ የፎስፈረስ ቀመር ባህርይ ያለው ነው። ሁለተኛው ጠቃሚ ቡድን ደግሞ ካምቢሶል (Cambisol) ሲሆን ጥልቀት የሌለው ድንጋያማና በንጥረ ነገር ይዘትም በተለይ የፎስፈረስ ይዘቱና (Organic matter) ዝቅተኛ ነው። እንደዚሁም ውሀ የመቋጠር ችግርና የናይትሮጂን እጥረት በአንዳንድ የአፈር ዓይነቶች ላይ የሚታይ በመሆኑ ለአዝርዕት ምርታማነት ዋንኛ ማነቆዎች ናቸው።

የተጠናከረ የማዳበሪያ ተጓዳኝ ምርምር ማካሄድ በእርሻው ዘርፍ የማዳበሪያ መጠንና አጠቃቀም ለማስደግ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ስለሆነም ብሔራዊ የግብርና የምርምር ሥርዓት (ብግምሥ) በአፈር ለምነት ምርምርና የማሻሻያ ተግበሮች ላይ ትኩረት እንዲሰጥ ይደረጋል።

28. <u>የኬሚካል ማዳበሪያ</u> ናይትሮጂን እና ፎስፈረስ እንደቅደም ተከተላቸው በኢትዮጵያ አፈሮች ውስጥ እንደ ዋንኛ የምርት ማነቆ የዕፅዋት ንጥረ ምግቦች (Nutrients) ይቆጠራሉ። ስለዚህ እነዚህን ምግቦች በዋናዋና አፈሮችና የአዝርዕት ምርቶች እንዲሁም በተለያዩ የግብርና ሁኔታዎች ውስጥ ለማሻሻል ጥረት ይደረጋል።

29. ሀገራቱ ለማዳበሪያ ዝግጅት የሚረዱ በቂ ጥሬ ሀብቶችና ሌሎች አግሮ ማዕድናት ማለት እንደ ፎስፌት ድንጋይ፣ የኖራ ድንጋይና ጂፕሰም የመሳሰሉ አሏት። የእነዚህ ሀብቶች አስተዋጽኦ፣ ከአፈ ንጥረ ምግብነትና በአካበቢ ላይ ሊኖራቸው ከሚችለው ተጽዕኖ አንፃር፣ የአፈር፣ የእጽዋትና የውሀ ጥናት መመዘኛ ነጥቦችን በመከተል ይገመገማሉ።

30. <u>በዮ ማዳበሪያዎች፣</u> መሬትን ምርታማ የማድረጉ ፕሮግራም የሚመሰረትበት መርሀ፣ ምግብና የመኖ ሊጊዩም /ቅጠላቅጠል/ እንዲሁም ሁለገብ-የሌጊዩም ዘሮችን እንደ አነስተኛ ዋጋ ያላቸው የናይትሮጂን ምንጮች አድርጉ በመውሰድ ይሆናል።

ስለሆነም የላቀ ጠቀሜታ ያላቸው የሥራ ሥር ተክሎችና ሌሎች ጠቃሚ ጥቃቅን ነፍሳት፣በተለያዩ የአፈር ሁኔታዎች ውስጥ ይጠናሉ ፣ ያድጋሉ እንዲሁም ለአገልግሎት እንዲቀርቡም ያደርጋል።

31. በየአካባቢው የሚገኙ ኦርጋኒክ የማዳበሪያ ምንጮችን፣ ለምሳሌ የከብቶች እበት፣ የባዮ ጋዝ ቅሪት፣ የቂራ ተረፈ- ምርት፣ ብስባሾችና የሰዎች- እዳሪን፣ በመጠቀም በኬሚካል ማዳበሪያ ላይ ያለንን ጥገኝነት ለመቀነስና በአንፃሩም እራስን ለመቻል፣ የራሳችንን ሀብት በማበልጸግ፣ የውጪ ምንዛሪ ወጪያችንን ለመቀነስ ጉዳዩ ትኩረት ይሰጣል።

32. <u>የአሠራር ልምድን ማሻሻል፣</u> የኢትዮጵያ ገበሬዎች ልምድ ለዘመናት የተዋሐደ የእጽዋትና እንስሰት ግብርና በመሆኑ ምርታማነት እንደይቋረጥ ረድቷቸዋል። ይሄ የገበሬው ልምዳዊ እውቀት ማለት እጽዋትና እንስሳት ከዝጉ የንጥረ-ምግብ ኡደት(closed nutrient cycle) በጋራ ተጠቃሚ የሆኑበት ስርዓት ሊያድግና በአግባቡ ጥቅም ላይ ሊውል ይገባል።

33. በማዳበሪያ ሳቢያ አዝርዕት የሚሰጡት ውጤት የሚነቃቃው፣ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴን ከመጠቀም በተጨማሪ በባዮቲክና አባዮቲክ /ህይወት ካላቸውና በሌላቸው ጥቃቅን ነፍሳት/ ነገሮች መብላላት ሂደትም ነው። ስለሆነም ከማዳበሪያ የሚገኘውን ውጤት፣ ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ የሚታዘዙትን የቴክኒዎሎጂ ፓኬጆችን/ ለምሣሌ ከፍተኛ ምርት ሰጪ ዝርያዎች እና የአዝርዕት ልማት የተሻሻሉ አሠራሮችን/ በሚገባ በመጠቀም ይሆናል።

34. የማዳበሪያን አጠቃቀም ደረጃ ለማሣደግ፣ የመሬትና የውሀን አያያዝ ልምድ ማሰደግ ያስፈልጋል። የማዳበሪያን አጠቃቀም ደረጃ ከፍ ለማድረጉና ዘለቂ የግብርና ምርታማነትን ለማስገኘት፣ ጠቃሚ የሆኑ የአፈር አጠባበቅ ቴክኒኮችና ተስማሚ የውሀ አጠቃቀም ልምዶችን ተግባራዊ በማድረጉ ላይ ትኩረት ይሰጣል።

35. የተሻሻለ የአስተራረስ ዘዴ፣ ሁለገብ አስተራረስ፣ የአዝርዕት ፈረቃ እና ግሪን ሚንዩሪንግ /የአረንጓዴ ተክሎች ብስባሽ ማዳበሪያ/ የአፈሩን የማምረት አቅም በማሻሻል፣ የአዝርዕት ምርታማነትን ለማሰደግ የሚረዱ ጠቃሚ ዘዴዎች ናቸው። ስለሆነም ያልተቋረጠ የማምረት ሂደትን ለመጠበቅ ሲባል የተሻሻለ የአስተራረስ ልምድ ለተለያዩ አግሮ-ኢኮሎጂ ሁኔታዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

36. በመካሄድ ላይ ባለው ዝርያዎችን የማዳቀል ብሔራዊ ጥናት፣ የአዝርዕት ዝርያ አይነቶችንና የተክል ቻግኝ አይነቶችን /ካልቲቫር/ በማሻሻል፣ ሰፊ ተሞክሮ

<u>የማደበሪያ ኤክስቴንሽን፤</u>

37. ኤክስቴንሽን በአጠቃላይ ማደበሪያን በማስተዋወቅና ተቀባይነትም በማስገኘት ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በመሆኑም፤ በአሁኑ ጊዜ የማደበሪያ ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በተለያዩ የአቀራረብ ስልቶች እየተካሄደ ይገኛል ። ሆኖም እነዚህን የተለያዩ ፕሮግራሞች የተሻሉ ለማድረግ ፤ ተግባሮቻቸውን ባለው አጠቃለይ ብሔራዊ የግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓት ውስጥ መልክ ባለው ሁኔታ ማደራጀትና ማቀናጀት ያስፈልጋል። ይህም በመሆኑ፡-

ሀ/ መንግሥት በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ በምግብ እራስን የመቻል ብሔራዊ ዓለማውን ለማሳካት በማደበሪያ ኤክስቴንሽን በኩል፤ ቅድሚያ ሊሠጣቸው የሚገቡ ክልሎችና ስትራቴጂያዊ ምርቶችን ይለያል፤

ለ/ በክፍለተ ኢኮኖሚ መካከል መደጋገፍ መኖሩ፤ ለገጠር ልማት በአጠቃላይ ለሰብል ምርታማነት በተለይ፤ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ከምርት ማስደጊያ አቅራቢዎችና ከሌሎች መሰል ድርጅቶች ጋር ለሚኖረው መቀራረብም ዋስትና ይሠጣል።

ሐ/ የማደበሪያ ጠቀሜታ ተቀባይነትን እንዲያገኝ፤ በተሻሻሉ የአግሮኖሚ ፓኬጆችና በተጠኑ የአፈር ምርምር ውጤቶች ላይ ተመስርቶ ስፊ መሬት በማልማት በሚተደደሩ አርሶ አደሮች ሰፋፊ ማሳዎች ላይ የሠርቶ ማሳያ ፕሮግራሞች ይካሄዳሉ። ብሔራዊና ክልላዊ የመገናኛ ብዙሐን አገልግሎቶችም ጥቅም ላይ ይውላሉ፤ ገበሬዎች ልምዳቸውን እንዲያሠራጩ ተሰታፊ ይሆናሉ።

መ/ በኤክቴንሽን /የልማት/ ወኪሎች ምርጫ ወቅትም ስለ ገጠሩ ሕይወት ልምድ ያላቸው የኅብረተሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችን የተገነዘቡ መሆናቸው ይረጋገጣል።

ሠ/ የልማት ወኪል-ገበሬ ቀመር የሥራ አፈጻጸማቸውን ለማሻሻል ሲባል ቁጥራቸው በተመጣጣኝ ደረጃ እንዲጨምር ይደረጋል።

ረ/ ጠጣታማ የሆነ የግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓት ለመፍጠር ብቃት ያለው የአማካሪ አገልግሎት፤ የሰለጠነ የሰው ኃይል፤ በቂ የሆኑ የሥራ መሣሪያዎችና የማነቃቂያ ስልቶችን፤ በኤክስቴንሽን ተግባር ለሚሰተፍ ሁሉ ለመስጠት ጥረት ያደርጋል።

## ክፍል ዘጠኝ

## የማደበሪያ ጥራት ቁጥጥርና የአከበቢ ጥበቃ

38. ማደበሪያዎችን አለአግባብ መጠቀሙ የአፈሩን ሁኔታ በመበከል የአካባቢውንም ሚዛን ወደ ማዛባቱ ሊያመራ ይችላል። በተጨማሪም የእርሻ መሬቶችንና ሌሎች ከበቢ ሁኔታዎች በማሳጣት የአየር ሁኔታ መዛባትና የከርሰ ምድርና የገጸ-ምድር ውሀን መበከል ያስከትላል።

### የጥራት ቁጥጥር

39. ማደበሪያ አስፈላጊ ሸቀጥ የመሆኑን ያህል ተጠቃሚዎችም በደንብ እንዲገነዘቡ ባለመደረጉ፣ የምርቱን ጥራት ለመቆጣጠር /መርምሮ ለማወቅ/ የሚረድ መሣሪያዎችም የሉም ስለሆነም መንግሥት ማደበሪያ ወደ ሀገር በሚገበበትም ጊዜም ሆነ በስርጭቱ ሂደት ጥራቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል ህግ ማውጣት አለበት። የጥራት ቁጥጥር ሲባል፣ (i) የምርቶቹ /የሩብሪካ ውጤቶችን/ ንጥረ-ነገር ይዘት (ii) የገጽታዊ-ጥራት መቀነስ (iii) በማስገባቱና ማሰራጨቱ ሂደት በምርቱ ላይ የሚፈጠር ማጭበርበርንም /ከሌላ ጋር አደባልቆ/ ያካትታል።

40. መንግሥት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ ማደበሪያዎችን ገበሬዎች እንዳይጠቀሙ ይጠብቃል። ስለሆነም የገበሬውን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

    ሀ. ትክክለኞቹ የማደበሪያ አይነቶች መሆናቸውን ለማረጋገጥና ዋስትና ለመስጠት የመመርመሪየ መሣሪየዎች መኖር የማይታለፍ ጉደይ ነው። ስለሆነም ብቃት ያለውና አስተማማኝ አገልግሎት ለመስጠት፣ ጥራትን በማረጋገጡ መስክ፣ የምርመራ አቅምን ለማሰደግና ለማጠናከር ጥረት ይደረጋል።

    ለ. ጥራት ያለጡ የማደበሪያ አቅርቦት መኖሩን ለማረጋገጥ፣ በሁሉም ደረጃ ጠለቅ ያለ ፍተሻ በማድረግ የጥራት ቁጥጥር ስርዓትም ይጠናከራል።

    ሐ. ገበሬዎች በተጭበረበሩ የማደበሪያ ምርት አይነቶች እንዳይታለሉ ስለ ማደበሪየ ጥራት ጉደይ ያላቸውን ዕውቀት እንዲየሰድጉ በማድረግ ቀለል ያሉ የጥራት ቁጥጥር ተግባራትን እራሰቸው እንዲየከናውኑ ይበረታታሉ።

    መ. በአሁኑ ጊዜ ያለውን የማደበሪያ ደረጃ ቁጥጥር በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል።

<u>የአከባቢ ጥበቃ</u>

41. የመከላከል እርምጃ ከልተወሰደ በቀር አካባቢዎች እጅግ አስከፊ በሆነ ሁኔታ፣ አግባብ በሌለው የማዳበሪያ ውጤቶች አጠቃቀምና የኢንዱስትሪ ዝቃጮች እየተ ጎዱ ናቸው። በዚህም ሰቢያ ለማዳበሪያ ውጤቶችና በሀገር ውስጥ ለሚቋቋሙ የማዳበሪያ እርሻዎች የሚሆን የአከባቢ መመዘኛዎች ወጥተው ሥራ ላይ ይውላሉ። በመሆኑም፣

ሀ. የንጥረ-ነገሮች ብክነትን ለመቀነስና ሌሎች በአካባቢ ላይ የአየር ብክለ የሚያስከትሉ ነገሮችን ለመከላከል፣ ብቃት ያለው የአሠራር ስልት ለማስተዋወቅ፣ ለማራመድና ለመጠቀም ጥረት ይደረጋል።

ለ. የአፈርን ይዘትና የአካባቢን ሁኔታ መናጋት የሚያስከትሉ የማዳበሪያ ቁሶች በጥንቃቄ ይገመገማሉ፣ ተለይተው ይወጣሉ፣ እንደፈስፈለጊነቱም ይታገዳሉ።

ሐ. የማዳበሪያ ጥሬ ሀብቶችና ሌሎች የግብርና ማዕድናት ፍለጋ ቁፋሮዎች፣ ፋብሪካዎችና፣ አጠቃቀሞች ይመረምራሉ፣ ይገመገማሉ፣ በተጨማሪ ለማዕድን ፍለጋ የተቆፈሩና፣ የተናጉ አከባቢዎች መልሰው እንዲያብቡና እንዲያገግሙ ይደረጋል።

መ. ብልሀነት የሌለበትና ከመጠን ያለፈ የማዳበሪያዎች አጠቃቀም በረጅም ጊዜ ሂደት የገጸ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሀዎች ብክለ ያስከትላል። አከባቢዎችንም በስፋት እንዲሁ። ስለሆነም በውሃ፣ በምግብ ምንጮችና በአፈሮች ንጥረ ነገር ይዘት ላይ ቁጥጥር /ግምገማ/ ይደረጋል።

ሠ. የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂና ዕፅዋቶች የሚገኙበት ሥፍራ፣ በአከባቢ ሁኔታ ላይ የማይናቅ ተፅዕኖ አላቸው። ስለሆነም፣ ለአከባቢዎች ዋስትና ያለው ቴክናሎጂና የዕፅዋት ሥፍራ መረጣ ይከሄዳል።

ረ. ከማዳበሪያ መፈብረኪያ ሆእርሻ የሚወጡ ዝቃጮችና ሽታዎች ከመለቀቃቸው በፊት በአግባቡ እንዲያዙ /ተጽእኗቸው እንዲቀንስ/ ይደረጋሉ።

ሰ. ስትራቴጂያዊ በሆኑ ሥፍራዎች ለአካባቢ ጥበቃ የሚያገለግሉ የቁጥጥርና የምርመራ አገልግሎቶች እንዲቋቋሙ እርምጃ ይወሰዳል።

ሸ. ማዳበሪያዎችና ሌሎች ነገሮች በአካባቢ ላይ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ ለመቆጣጠር ለዳታ ቤዝ ጥንቅርና አያያዝ ተግበር እርምጃ ይወሰዳል። እንዲሁም፣

ቀ. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የማዳበሪያ አይነቶች በብሔራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓት /ብግምሥ/ National Agricultural Research system (NARS) ፈቃድ/ ትዕዛዝ ላይ የተመሰረቱ መሆን ይገባቸዋል።

## ክፍል አሥር

## ብሔራዊ ማዳበሪያ ኢንዱስትሪ አደራጃጀት

42. ብሔራዊ የማዳበሪያ ፖሊሲ ባለመውጣቱና የማዳበሪያን እንቅስቃሴዎች በኃላፊነት የሚመራና የሚያስተባብር መንግሥታዊ ድርጅት ባለመኖሩ ሰቢያ የንዑስ ዘርፉ እድገትና ልማት ተገቶ ቆይቷል። ስለሆነም ንዑስ-ዘርፉን ለማልማት እንዲቻል የሚመለከታቸው ድርጅቶች ተግባሮቻቸውን የሚያቀናጁበት የተቋሞች ስብስብ ያለበት አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆነዋል። በዚህም ሰቢያ ብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ቦርድ /ብማኢቦ/ (NFIB) እና በሥራ አስፈጻሚነትም ብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ /ብማኢኤ/ (NFIA) ይቋቋማሉ። በሔራዊ የማዳበሪ ኢንዱስትሪ ቦርድ የሚያካትታቸው አበላት፣

| | |
|---|---|
| ሀ. የግብርና ሚኒስቴር | ሰብሳቢ |
| ለ. የተፈጥሮ ሀብት ልማትና የአካባቢ ጥበቃ ሚኒስቴር | ፀሐፊ |
| ሐ. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | አባል |
| መ. የማዕድንና ኃይል ሚኒስቴር | " |
| ሠ. የትራንስፖትና መገናኛ ሚኒስቴር | " |
| ረ. የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን | " |
| ሰ. የኢትዮጵያ ደረጃዎች መደቢ ባለሥልጣን | " |
| ሸ. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ | " |
| ቀ. ሶስት እጩቅ ሳይንቲስቶች | " |
| በ. የክልለ ጉዳዮች ዘርፍ ጽ/ቤት | " |
| ተ. ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ | " |

43. ብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ቦርድ / ብማኢቦ/ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

ሀ. የፖሊሲ ሐሳቦችን ያቀርባል፣ ማናቸውንም የማዳበሪያ አጠቃቀምና ልማት ጉዳዩችን በተመለከተ መንግሥትን ያማክራል፣ ብሔራዊ የማደበሪያ ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግበር ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።

ለ. ለተስተካከለና ስርዓት ላለው የማስገባትና የማስጠጣት እንዲሁም የማሰራጨት፣ በተጨማሪም ሀገረኛ የማደበሪያ ኢንዱስትሪ ለማቋቋም የሚረዱ መመሪያዎችንና የአሠራር ስርዓቶችን ያወጣል።

ሐ. ስለማዳበሪያ አጠቃቀምና ልማት የሚወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ የሀገሪቱን አጠቃለይ ብሔራዊ ዓላማ የጠበቀ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

መ. የማዳበሪያ አጠቃቀምና ልማት ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን ከሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት፣ ይገመግማል፣ ያጠናል፣ ያሻሽላል።

ሠ. በማንኛውም መስክ ንዑስ-ዘርፍ ብቃት የሚያ ጐለብት እርምጃ ይወስዳል።

ረ. ለኤጀንሲው የሥራ እንቅስቃሴ የሚረዱ መመሪያዎችን ያወጣል፣ ሥራውንም ይመራል።

44. <u>ብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ</u>፣ የብሔራዊ ማዳበሪያ ኢንዱስትሪ በርድ፣ ሥራ አስፈጻሚ የሆነው ብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፣

ሀ. ይህ የማዳበሪያ አጠቃቀምና የልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ሌሎችንም ተግበራት ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

ለ. የማዳበሪያ ንዑስ-ዘርፍ እንዲያድግና እንዲለማ ያበረታታል፣ ለግብርና ምርት እድገትም የ ጐላ ተሰትፎ ያደርጋል።

45. <u>የብሄራዊ ማደበሪያ ኤጀንሲ / የብማ ኢ ኢ/ ተግበርና ኃለፊነት</u>

ሀ. ከማዳበሪያ ጋር ተዛምደ ያላቸውን ወደ ሀገር የማስገባትና የማስወጣት፣ የጥሬ ሀብት ልማትና ሌሎች ተግበራትን በሚመለከት የወጡ ሕጐችና መመሪያዎች በአግበቡ ሥራ ላይ መዋለቸውን ይቆጣጠራል፣ ያረጋጋጣል።

ለ. ለውሳኔ ሰጪዎችና ለሌሎች፣ ስለ አለም አቀፍ የማዳበሪያ ፍላጐትና /አቅርበት ሁኔታ፣ ስለ ዋጋና የምርት ማሣደጊያዎች ወጪ፣ እንዲሁም ስለ ሀገር ውስጥ ፍጆታ፣ ወቅታዊ መረጃዎችን ይሰጣል።

ሐ. ከእርዳታ ሰጪዎችና ከሌሎች የፋይናንስ ተቋሞች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ይፈጥራል።

መ. በዘርፍ ለተሰማሩ ባለምያዎች የስልጠናና የጉብኝት ኘሮግራም ያዘጋጃል።

ሠ. መንግሥትን በመወከልና ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋሞች ጋር በመተበበር የማደበሪያ ብድርና እርዳታዎችን በተመለከተ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ድርጅቶች ጋር ይደራደራል፣ ስምምነቶችንም ይፈርማል።

ረ. የማዳበሪያን አጠቃቀምና ልማት ለማሳደግ የሚረዱ ሌሎች አስፈላጊ ተግበሮችንም ያከናውናል።

46. <u>የብማ ኢ.ኢ. ዋና ሥራ አስኪያጅ ተግበርና ኃላፊነት፣</u>

ሀ. የአጭር የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ የሥራ ፕሮግራም ያወጣል፣ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን ገምግሞ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በሥራ መተርጐማቸውንም ያረጋግጣል።

ለ. የማዳበሪያ ንዑስ-ዘርፍ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

ሐ. በማዳበሪያው ንዑስ ዘርፍ ንቁ ተሳትፎ ከሚያደርጉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ጥሩ የሥራ ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋል።

መ. ኤጀንሲውን በሶስተኛ ወገን በመወከል ማንኛውንም ስምምነት ይፈርማል፣እንዲሁም ኤጀንሲውን በሚመለከትም ውል ይፈጽማል።

47. <u>የማዳበሪያ ዳታ-ቤዝ፣</u> /የመረጃ ጥንቅርና ትንተና/ በብማ ኢ.ኢ. ተቆጣጣሪነት ሥር የተጠናከረ ብሔራዊ የማዳበሪያ መረጃዎች ዶክመንቴሽን ስርዓትን በማቋቋም ለንዑስ ዘርፍ ልማት የሚረዱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያሠራጫል።

48. <u>የማዳበሪያ ሕግ፣</u> የማዳበሪያን ንግድ ለማበረታታት፣ የጥራት ደረጃን ለማረጋገጥ እና የተጠቃሚዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ መንግሥት ብሔራዊ የማዳበሪያ ሕግ ያዘጋጃል፣ አዋጅም ያወጣል።

49. <u>የብሔራዊ ማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር</u>፣ ብቃት ያለው ብሔራዊ መመሪያ እና በተቋሞች መካከል የትብብር ሰንሰለት በለመኖሩ ሳቢያ፣ ለማዳበሪያ አጠቃቀምና ልማት እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል። ይህንን ቅግር ለመወጣት በኤጀንሲው ውስጥ የሚከተሉትን ክፍሎች ማቋቋም አስፈላጊ ይሆናል።

ሀ. የገበያ ጥናትና ልማት
ለ. ክትትልና ግምገማ
ሐ. የጥራ ሀብት ልማት

50. የነዚህ የልዩ ልዩ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት በብሔራዊ የማዳበሪያ እንዱስትሪ በርድ የሚወጣ ይሆናል።